# <u>የሰላም ትግል በመደራደር - ስምምነት ወይስ በምን?</u>

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ወዳድ፣ ቻይና፣ ታጋሽ፣ ትሑት የሆነ ለዘመናት በኅብረት ጎን ለጎን ሲኖር የቆየ አዋቂና አስተዋይ ሕዝብ ነው። ሕዝቡ ተከባብሮና ተቻችሎ አብሮ ለመኖርና ለመበልጸግ ጽኑ እምነትና ፍላጎት ያለው ነው። የሕዝቡ ጩኸት እንስማማ፣ እንቀራረብ፣ እንቻቻል፣ እንግባባ፣ በእኩልነት አብረን በመኖር እንደግ ነው።

ለኢትዮጵያ ዋነኛው ችግሯ ይህን የሕዝብ አንድነት ታሪክና ጥንታዊነት ወደ ዘመናዊ አስተማማኝ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለመመንዘር አለመቻሏ ነው። የፖለቲካ ሥርዓቱ ትናንትም ሆነ ዛሬ ኋላ ቀር በመሆኑ ሰላምና መረጋጋት ማስገኛ ሆኖ ሊያገለግል አልቻለም። ሕዝቡ ለዘመናት የፈላጭ ቆራጮች መፈንጫ ሆኖ ለረጅም ጊዜ ተንገላቷል፣ ፍትህ አጥቶ ተሰቃይቷል፣ ዕድሜ ልኩን ተገኘር ሆኖ ፍዳውን አይቷል፣ እያየም ነው።

የሃገራችን ኢትዮጵያ የኑሮ ሁኔታ፣ የኢኮኖሚው፣ የፖለቲካው ውጣ ውረድ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሳለፈው የረዥርም ጊዜ የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ ሲታገልበት ሲደማበት የኖረውን የሕዝብ ስልጣን አመንጭነት፣ ባለቤትነት እና ተቆጣጣሪነት መብት እውን ለማድረግ ለኢትዮጵያኖች ወቅታዊ አንገብጋቢ ጥያቄና ዋና ችግሮች ናቸው። በዚህ ሁኔታ የኛ የዜጎቿ ፈንታ አሁን መላው የኢትዮጵያዊ አንድነት ፓርቲ (ቅንጅት /መኢአድ) ከገዥው ፓርቲ ጋር በመደራደር የተገኘውን ዕድል በከፍተኛ እና በዋናነት ተገንዝበን እንደ አስፈላጊነቱ እና በበቂ መልክ መጠቀም ያለብን ይመስለኛል።

መኢአድ ከገዥው ፓርቲ ከኢሃዲግ ጋር መደራደርና ስምምነት ተደርሶ የፓርቲዎች ስነ ምግባር ሰነድ በመኢአድ ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ ኃይሉ ሻወል የተፈረመው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተፈጸመው መጥፎ በደል እና በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው ጉዳት ተረስቶ ሳይሆን ይቅር ለእግዚአብሔር ለምህረትና ሰላም መርሆ “We can never forget but we can forgive” principle የሕዝብ ዲሞክራሲን፣ የሕግ የበላይነትን ስርዓት መመስረት አማራጭ የሌለው የሕዝብ ወቅታዊና ዘላቂ ጥያቄ መሆኑን ምላሽ ያገኝ ዘንድ በመገንዘብ ነው። የሚካሄደውም የሰላም ትግል ነው። የሰላም ትግል ምን ማለት ነው? መልሱን ለአንባቢያን እተዋለሁ።

ሰሞኑን የሚወራውና የሚጻፈው ይህን የተገኘ ዕድል መቃወምና የአፍራሽነት መንፈስ ስለሆነ ቢቆም መልካም ነው። ነገሮችን በቅን፣ በሰከነ አንደበት ዓይተንና ተረድተን ለፍጻሜነታቸው በኅብረት ብንገፋ ኅብረተሰባችን በዚህ ሊያደርግ የሚችለውን ብንጠብቅ ጥሩ ነው። በእኔ አስተያየት የተነጋገሩባቸው ነጥቦች የተፈረመው ሥነ-ምግባር ሰነድ አንዳንዶች እንደሚቃወሙት፣ እንደሚሉት፣ እንደፃፉት፣ ማንበብና መስማት ሳይሆን እራሴን የችግሩ አካል በማድረግ አንገብጋቢ ብዬ የማየው ኢሃዲግ /ሕዋሓት የሰራውን ጥፋት መጥፎ በደል ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ ስምምነት በመነሳት በምርጫ ምን ያገኛል ነው። እንደ ዕውነት ከሆነ ይህ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ የለውጥ ዕድል ነው። ያለ ምንም ጥርጥር የማይመለስ የወደፊት የትግል መስመር ምዕራፍ ነው።

ስለዚህ እኔ ለሃገር ለወገን ወዳድ ኢትዮጵያኖች የምሰጠው ምክርና አስተያየት ይህ የተፈራረሙበት ሰነድ እጅግ አስፈላጊነቱን አንብቡና ተረዱት የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አካል እንድትሆኑ አቋማችሁን እንድትወስኑ ይረዳል ነው። እስቲ ራሳችንን እንጠይቅ ምን ልዩ ነገር እንዲደረግ እንፈልጋለን? በእውነት ምን እንደምንፈልግ እናውቃለን? እንዴትስ እናገኘዋለን? በርግጥ ከአሰብነውና በጥልቀት ከተረዳነው ይህ ስምምነት በሁለት ሺህ ሁለት (2002) ግንቦት ምርጫን በማሸነፍ ፣ የሕዝብ ስልጣንን ማግኘትና በኢሃዲግ የተገደሉ ዜጎቻችንን ድል አድራጊነት

የሚበሰርበት ነው። የታሰሩና ያለ ሕግ የሚንገላቱ ዜጎችን የምናስፈታበት ዋስትና ነው።

የዚህ የፓርቲዎች ሥነ ምግባር ሰነድ ዛሬ መፈረም የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ችግር የልብ ትርታ ስሜት መሰበርና የተስፋ ማሳጠት አይደለም። በተቃራኒው የሰነዱን ምንነትና ሁኔታ ሳታውቁና ሳትረዱ ሳታነቡትም ጭምር ደረት ለምትመቱና አሉባልታ ለምታናፍሱ ትዕግስትና አስተዋይነትን፣ የሰከነ አንደበትና አመለካከት እንዲኖራችሁ እጠይቃለሁ።

አንድ ዜጋ ለአገሩ ለወገኑ በቅንነት በቆራጠኝነት፣ መቆምና መታገል ከሌሎችም ጋር መተባበር ይኖርበታል። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ በባህል በጋርዮሽ ኑሮ የበለጸገች የብዙ ሺ ዓመት ማህበራዊ ኑሮ ያላት አገር ዜጋ ለአነጋገሩ፣ ለአስተያየቱ የሰከነ አንደበት ያለው፣ ትዕግሥትን ባህሪ ያደረገ ከመናገር መስማትን (መናገር ብር ነው ዝምታ ግን ወርቅ ነው) መርሆ ተከትሎ እውቀትንና ጥበብን የሚቀስም (የሚገኝ) መሆን አለበት። እውነትን የያዘ ዕውቀት፣ ጥበብ የሚሻ የሚፈልግ እንጂ ብዙ ያልሆነና በሃሰት አሉባልታ ከሃቅ የራቀ የሚያናፍስና ተሳስቶ የሚያሳስት መሆን የለበትም። ኢትዮጵያኖች በዓይናቸው ካላዩ፣ በጆሮአቸው ካልሰሙ፣ መረጃ ካላገኙ፣ አያምኑም አያወሩም ይባል ነበር አሁን ግን የማናውቀውን፣ ያልሰማነውን፣ ማንበብ ስንችል ያለነበብነው፣ ያላየነውን ጨምረንና ጨማምረን የምናወራ የአሉባልታ ሰዎች በዝተናል። ኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ፣ አስተያየት፣ ወግና ባህላዊ ግንዛቤ ቢኖረን ያስከብረናል ያኮራናል እና መልካሙን አስበን በኢትዮጵያዊነታችን እንታፈር እንኩራ።

ሰው በራሱ ላይ መፍረድ እንጂ በማያውቀው በሌለው ሰው ላይ አይፈርድም። ሰው ራሱ ማን? ምንድንና? ምን? የሚያደርግ መሆኑን ማወቅና መረዳት አለበት። ከእምነት በፊት እውቀት ያሻል ያወቀ ደግሞ እውቀቱን ላላወቀው ያካፍላል ያሳውቃል። ብስለት ያነሰው ሰው ሁልጊዜ ስለ ሰው ያወራል አዋቂ ግን ስለ ተፈጥሮ፣ ስለ ፈጠራ፣ የሕዝብ ችግርና መፍትሔውን ይወያያል፣ ይሰራል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ኢሃዲግ/ሕዋሓትን ሕገ መንግሥት ተቀብለው ተቃዋሚ ፓርቲዎች በከፍተኛ ሰላማዊ ትግል እያደረጉ ነው። ይህም የሰላም ትግልን እውን ለማድረግ ነው በተቃራኒው የኃይል ትግልን በመተው። ስለዚህ ያላቸው ዋነኛውና ከፍተኛው መሳሪያቸው በሕጋዊ መንገድ እየተመሩ ምርጫን መጠቀም ነው። ያላቸው መሳሪያ የሕዝብ ምርጫ ነው። ለምርጫ መወዳደር እና መካፈል ያስፈልጋል ምርጫ የሰላም የትግል መሳሪያ ስለሆነ። በሰላም እንታገላለን ያሉ በኢትዮጵያ ሜዳ ላይ ያሉና ትግሉ በሚካሄድበት ቦታ የተገኙ ምርጫቸው ሕግን ተቀብሎና ተስማምቶ በምርጫ በመሳተፍና ለማሸነፍ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ነው። ይህ ነው በኃይል የመጣውን አስተዳደር የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊላቀቅ የሚችልበት ዋና መሣሪያ የሰላም ትግል ይህ ካልሆነ ምን መሆን አለበት? በምርጫ ለለመሳተፍ ረግጦ መውጣት ዲሞክራሲያዊ መንገድ ካለመሆኑም ለወያኔ ሜዳውን ጥሎ እንደ መውጣት ነው።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ በደንብ ጠልቀው በመግባትና በምርጫ ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ የተገኘውን ዘዴና መንገድ ተጠቅመው ይህን በኃይል የመጣ አስተዳደር ለመቀየር የሚያጋጥማቸውን መሰናክል ለማለፍ አመቺውን ሕጋዊ መሣሪያ ሁሉ መጠቀም ያስፈልጋቸዋል። ይህ ካልሆነ ርግጥ ነው ይህ ሊወድቅ የደረሰ የኢሃዲግ አስተዳደር ተቃዋሚዎች እንዳያሸንፍ የሚቻለውን መከላከል ያደርጋል። ሕዋሐት ያልተሳለ መሳሪያ ነው ስለዚህም ምርጫ በሕዝብ ኃይል ለማስወጣት ትግል ዋነኛው መሳሪያ ነው። ከዘወትር (conventional) የፖለቲካ ውድድር ባህሪ ሲታይና ሲነጣጠር በአንፃሩ የሁለት ሺህ ሁለት (2002) ምርጫ በምን አይነት ስርዓት መመራትና መካሄድ እንዳለበት በምርጫ የሚከፈሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ልዩና ግልጽ በሆነ መነጋገርና መስማማት፣ ከመጀመሪያው ከመወዳደር ጀምሮ እስከ ምርጫው መጨረሻ ድረስ

የሚመሩበት ከወዲሁ ማለምና ማቀድ፣ መስማማት ላይ መምጣት አስፈላጊ ነው።

ስለሆነም ሰሞኑን የምንሰማውና የምናየው የመፈራረም ሰነድ ልዩ የምርጫ ሥነ ምግባር ይህንኑ የፖለቲካ ትግልን የምርጫ መሳሪያነት የሚያሳይ የሰላም ትግል የእንቅስቃሴ ተግባር ነው። በእኔ ግምትና አስተያየት ይህ እጅግ የላቀ አጠቃላይ የታክቲክና ስትራቴጅ የማንኛውም የሰላም ትግል የፖለቲካ ፓርቲ ተጠቃሚነት ነው። የተነጋገሩበት፣ የተስማሙበትና የተፈረመው ሁሉንም አስፈላጊና ዋና ዋና ነገሮች የያዘና ያቀፈ ነው በዚህም መኢአድ ትልቅ አስተዋጽኦ ስለአደረገ ሊመሰገንና ሊወደስ ይገባዋል። ሌሎች ፓርቲዎችም ይህን በቅድሚያ በመደራደሩ እሰየሁ ሊሉ ይገባል እንጂ አያስቆጣም።

የተቃዋሚ ፓርቲዎች የገዢውን ፓርቲ ኢህአዲግን/ሕዋሓትን ለመቋቋም በርግጥ ከታሰበበት የሚቻለው ማንኛውንም መስዋዕትነት በመክፈል የተስማሙበት አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ በሕጋዊነት ለምርጫ መሳካት እንዲሟሉና እንዲሳኩ ገዥውን ፓርቲ ወጥሮ በመያዝና እንዲፈጸሙ ማድረግ ነው። የምርጫ ሂደት ከመጀመሪያ ዝግጅትነት እስከ መጨረሻው የምርጫ ቀን ጥረትን በከፍተኛ ኃይል የሚጠይቅ ነው። ይህም ሂደት ሰላምንና ደህንነትን በእጅጉ ይጠይቃል። በምርጫው ጊዜና ከምርጫም በኋላ የገዢው ፓርቲ የገባውን ቃል ባያሟላ ስምምነቱንና የተፈረመው ሰነድ ውል እንደፈረሰ ተቆጥሮ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከሕዝብ ጋር በሰላማዊ መንገድ ተቃሞአቸውን በማንሳት፣ የሕዝብ አመጽ እንደሚያስከትል ለዓለም ኅብረተሰብ በማሳወቅ ገዢው ፓርቲን ማጋለጥና የሕዝብ ትግሉን ያለ ማቋረጥ ማፋፋም፣ ማያያዝ አለባቸው።

አሁን ግን በሁለቱም በኩል በገዢው ፓርቲ እና በተቃዋሚ ፓርቲዎች ይህን መደራደርና ስምምነት አክብሮ ለፍፃሜነቱ በህብረት መስራት የሰለጠነ ፖለቲካ የሰላም ወዳድ ከመሆኑም በላይ ለሕግ ተገዥነትና የሕዝብን ስልጣንን ማክበርና መቀበል ነው። በመሆኑም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የሕዝብ ፍላጎትና ስሜት በድምጽ ተከብሮ የዲሞክራሲ ሥርዓት ማስመዝገብ ይሆናል ሕዝቡም በበኩሉ በዚህ ድንቅ ሥራ የሚኮራና፣ ለፓርቲዎች ምስጋና፣ አድናቆትና አክብሮት ሕያው አድርጎ በታሪክ ምዕራፍ ላይ ያስቀምጣል።

*ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር*
*በላይ መታፈሪያ*